# የእህት ኢዩሊአና ምስክርነት

(Testimony of Sister Iuliana)

እህት ኢዩሊአና እድሜዋ ወደ 76 ዓመት ገደማ ነበር። የተወለደችውም በሮማኒያ ነበር። አባቷ ኦርቶዶክስ ነበር። ኢዩሊአና ሕፃን እያለች ነበር የሞተው። ከዚያ ወደ በኋላ ላይ ካቶሊክ ሆነች። ሁል ጊዜም **የገነትን መንገድ** ትፈልግ ነበር። ወደ ማርያምና ወደ ቴሬሳ ጸለየች፥ ነገር ግን ጸሎቶቿ እንዳልተመለሱ ቀሩ። በውስጧ ነፍሷ ባዶነት ይሰማት ነበር። ክርስቲያን ለመሆን ትፈልግ ነበር፥ ነገር ግን ሰዎች ክርስቲያኖች እርኩሶች ናቸው አሏት። መዳንና ዘላለማዊ ሕይወት እንዲኖራት ትፈልግ ነበር።

ኢዩሊአና 7 ልጆች የነበራት ሲሆን በስጋጃ መሥሪያ ፋብሪካ ውስጥ ትሠራ ነበር። በጣም ደሀ ነበረች። አንድ ጊዜ ቆሻሻ ገንዳ ውስጥ ያገኘችውን የተከፈተ የቆርቆሮ ሥጋ በላች። ሥጋው ተበላሽቶ ነበር። በጣም ታመመች። ብዙ ሆስፒታሎች ወሰዷት። የጉበት ማበጥ በሽታ (hepatitis) ይዟት ነበር። ጉበቷ በጣም ተጎድቶ ስለነበር ሊያድኑት ምንም ማድረግ አልተቻላቸውም ነበር። ብዙ ክብደት ቀንሳ ነበር። 29 ኪ.ግ ብቻ ሆና ነበር። በመጨረሻም፥ ለ8 ወራት በየሆስፒታሉ ስትሠቃይ ቆይታ፥ ሞተች። ሰውነቷ በሬሳ ማቆያ ተቀምጦ ነበር። ነፍሷም በረዥም ሸለቆ ውስጥ ተወሰደ። ጨለማና ጭቃማ ነበር፥ በመንገዱም ድንጋዮችና እሾኾች ነበሩበት። በርቀት ብርሃን ይታያት ነበር። ወደ ብርሃን በፍጥነት ለመሄድ ፈለገች። ከጨለማውና በመንገዱ ካለው ድንጋይ የተነሳ በቀስታ ነበር ለመሄድ የተቻላት። (ይህ ኃይማኖቷን ያመለክታል) የሆነ ሰው እንድትመጣ ሲጠራት ሰማች፥ "*ነይ፥ ነይ ኢዩሊአና*"። በመጨረሻም በዋሻው መጨረሻ ስትደርስ፥ በጣም በተዋበ ቦታ ነበረች። ገነት ነበር። እንደዚህ ያለ ቦታ ከዚህ በፊት አይታ አታውቅም። በስሟ ሲጠራት የነበረው ሰው መልአክ ነበር። መልአኩም "*ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ማድረግ ስላለብሽ ወደ ምድር መመለስ ይኖርብሻል።*" አላት። መልአኩም ስሟን በሕይወት መጽሐፍ ላይ በፈለገ ጊዜ፥ ስሟ በውስጡ አልተጻፈም ነበር። መልአኩም ስለ **እግዚአብሔር አብና** ስለ **ልጁ** ስለ **ኢየሱስ**፥ ስለ24ቱ ሽማግሌዎችና ሁል ጊዜም **እግዚአብሔርን** ስለሚያወድሱት መላእክት አብራራላት።

በእውነት በዚያ መሆንን ፈልጋ ነበር፥ ነገር ግን አልተፈቀደላትም፥ ምክንያቱም በምድር ሳለች **ከእግዚአብሔር** ጋር ቃልኪዳን አላደረገችም። ለዘላለም በዚያ መሆንን ፈለገች። መልአኩ ለተወሰነ ጊዜ እንድትጠብቅ ነገራት። **ኢየሱስ** ከመላእክቱ ሁሉ ጋር በቤተመቅደስ ነበር። እያናገራቸው ነበር። ቤተመቅደሱ በብርጭቆ (በጠራ እቃ [crystal]) ነበር የተሠራው። ከቤተመቅደሱ በር ላይ፥ 2 መላእክት ተንበርክከው ነበር። **ኢየሱስ** ከመቅደሱ ወጥቶ እስኪመጣ ድረስ ዙሪያዋን ቃኘች።

የተዋቡ አበቦች በየቦታው ነበሩ። ሣሩ እንደ ሀር ያበራል። በጣም ረዥም ጠረጴዛ በዚያ ነበር። (የኪሎሜትር ያህል ርቀት ያለው ይመስል ነበር) ነጭ ጥልፍ የጠረጴዛ ልብስ ለብሷል። በጠረጴዛው ላይ ወተትና ማር ነበር፥ እንዲሁም ሌሎች ብዙ ዓይነት ፍራፍሬዎች። በጠረጴዛው እያንዳንዱ አቅጣጫ ወንበሮች ተቀምጠዋል። በጣም ረሀብ ተሰማትና ጥቂት እንጆሪ አልያም ወተት ለመውሰድ ፈለገች፥ ነገር ግን በጠረጴዛው ላይ ካለው ነገር ምንም መብት አልነበራትም።

ዙሪያዋን ተመለከተችና መንገዶቹ ሁሉ ከወርቅ እንደተሠሩ አስተዋለች። ቤቶቹ በወርቅና በብርጭቆ ነበር የተሠሩት። በዚያ ዛፎችም ጭምር ነበሩ። እያንዳንዱ ዛፍ የሚስብ ስም ነበረው። እያንዳንዱ ዛፍ የተለያየ ዓየነት ፍሬዎች ነበሩት። እንዲሁም በብርጭቆ የተሠራ ተራራ ነበር፥ በብራማ ዛፎች የተሞላ ደን ይገኝበታል። በዚያ እንሰሳትና ልጆችንም አይታለች። ልጆቹ ክንፍ ነበራቸው፥ እያንዳንዱም የዜማ መሣሪያን ይዘዋል። ልጆች ከእንስሳቱ ጋር ይጫወቱ ነበር። አንዳንዶቹም እንሰሳት በምድር ላይ አደገኛ እንደሆኑ አስተዋለች። ታላቅ ደስታ በዚያ ነበር። ሁሉም ደስተኛ ነበር። ከበሩ ላይ ተንበርክከው የነበሩት መላእክት እየተነሱ እንደሆነ አስተዋለች። በዚያ ሁሉም ነጭ ረዥም ልብስ ለብሰው ነበር፥ በራሳቸውም ላይ አክሊልን አድርገዋል። ፊታቸው በጣም ወጣት ይመስላል። እያንዳንዱም ለመቀመጥ ወደ ጠረጴዛው አመራ። ከዚያም ታላቅ ብርሃን ወደ እርሷ መጣ። ብርሃኑ እየቀረበ ሲመጣ፥ እየተንቀጠቀጠች ነበር በወለሉ ላይ ወድቃ ራሷን ሳተች። ከዚያም አንድ ሰው መጥቶ አነሣት። ሰውየውም ተናገራት። "***ወደ ምድር ሂደሽ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን አድርጊ። ስለአንቺም ጭምር ነው የሞትሁት። ለሁሉም ነው የሞትሁት። ላጣሽ አልፈልግም።***"

የያዛትና እያናገራት ያለው ማን እንደሆነ ለማወቅ ጓጉታ ነበር። በጨረፍታ ብቻ ለማየት ፈለገች። ነጭ የለበሰ ሰው ነበር። ባዶ እግሩንም ነበር። በእግሮቹ ላይ የሚስማር ምልክቶች ይታዩአታል። ፊቱ በብርሃን አስተላላፊ ሴራሚክ እንደተሠራ አሻንጉሊት (porcelain doll) ይመስላል። በርኅራኄ ተመለከታት፥ እናም በእርጋታ አናገራት፥ "*አንቺ ሴት ስላንቺ ሁሉንም አውቃለሁ፥ መከራሽን ሁሉ። ላጣሽ አልፈልግም። ከአብ ጋር ቃል ኪዳን ለማድረግ ወደ ምድር ተመለሽ። ምስክር እንድትሆኚ እፈልጋሁ። ማንም አላየኋትም ለማለት አይቻለውም።*"

ከዚያም ወደ ፍርድ ቦታ ተወሰደች። በዚህ ቦታ ሰባት ዳኞች ነበሩ። ከዚህ ሲዖል ይታያት ነበር። የአልኮል(መጠጥ)፣ ሲጋራ፣ ገንዘብ፣ ወርቅ፣ ውድ ልብሶች ክምር ይታያት ነበር። እነዚህን ነገሮች ሁሉ ይወዱ የነበሩ ሰዎች በሙሉ በግራ በኩል ነበሩ (በሲዖል)። ከእነዚህ ሰዎች ጋር ወደ ሲዖል ስለመሄድ አለመሄዷ እየተጨነቀች ነበር። ህይወቷን ሙሉ ተሰቃይታለች፥ በሕፃንነቷ ሳይቀር። በ7 ዓመት እድሜዋ የሀብታም ሰዎችን ላሞችንና በጎችን የምትጠብቅ ባሪያ(ገረድ) ነበረች። እግሮቿ በብርድ ተጠብሰዋል። በዚህም ምክንያት በእግሯ ላይ ችግር አለባት። ማንም አልራራላትም።

ሰዎች በሲዖል ሲጮኹ ትሰማ ነበር። አንዳንዶቹ "*ከንፈሮቻችንና ፊታችን እየተቃጠለ ስለሆነ ጥቂት ውኃ ብቻ። እርዱን፥ እርዱን።*" ይሉ ነበር። ልትረዳቸው ፈለገች። በዚያም ዛፍን አየች፥ ትቂት ሰዎችም ታስረውበት ነበር። በህይወታቸው የሆነ ጊዜ ውስጥ **እግዚአብሔርን** እንዳገለገሉ መናገር ትችል ነበር። አሁን ነጩ ልብሳቸው ቆሽሿል፥ እንዲሁም አክሊላቸው ተራግፏል። አሁን በሰይጣን እየተሰቃዩ ነው። አዘነችላቸው። ትጮኽ ነበር "*አትጉዷቸው፥ አትጉዷቸው!*" ሰዎቹን ጠየቀቻቸው፥ "*ነጩ ልብሳችሁ ምን ሆኖ ነው?*" እነዚህ ሰዎች የድሆችን ገንዘብ ወስደው ለራሳቸው ጥቅም እንዳዋሉ ተረዳች።

በዚያ የአፕል ዛፍን ተመለከተች፥ በላዩም አፕል ነበረበት። ከአፕሉም ጭማቂን ወስዳ ውኃን ለሚጠይቁት ሰዎች ልትሰጣቸው ወሰነች። አፕሉ ግን ደረቅ ነበር፥ በውስጡ ምንም ፈሳሽ አልነበረውም። ሁሉም ለእርዳት እየጮኸ ነበር። በምድር ውርጃን የፈጸመች እናት የከፋው ስቃይ ይደርስባት ነበር። በሰይጣን የልጃቸውን ሥጋ እንዲበሉ ይገደዱ ነበር።

በሲዖል ያሉ ሰዎች እያንዳንዳቸው በራሳቸው ጉርጓድ ውስጥ ነበሩ፥ እስከ ትከሻቸውም ይደርሳል። ከዚያ ሊወጡ አይችሉም። ሥጋቸው ከአጥንታቸው ሲለያይ ታይ ነበር፥ እንዲሁም ትሎችን በሰውነታቸው ላይ። ከ6 እስከ 8 የሚያህሉ ሰዎች ማረሻ ተጠምዶባቸው ነበር። እንዲጎትቱ ይገደዱ ነበር። ማረሻው በጣም ወደ መሬት ስለጠለቀ ለመጎተት በጣም አስቸጋሪ ነበር። ለመጎተት እየታገሉ ሰይጣን ይገርፋቸው ነበር። አዩሊአና ትጮህ ነበር፥ "*አትጉዳቸው፥ አትጉዳቸው!*"

አሁን የእርሷ የፍርድ ጊዜ ደረሰ። አንድ ሰው ኃጢአቱ ሳይገለጥ በፊት አይፈረድበትም። ትልቅ ስክሪን(ማሳያ) ነበር፥ ልክ እንደ ትልቅ መስታወት፥ የሰዎችን ህይወት የሚያሳይ። ጌታን ደስ ያላሰኙት ነገሮች ሁሉ ይገለጡ ነበር። የኢዩሊአናን ኃጢአቶች አሳዩ። አንዲት ሴት ልጅ መጥታ እንዲህ አለቻት፥ "*እናቴ፥ ለምን ገደልሺኝ፥ ስም እንኳን አላወጣሽልኝም ነበር። ነብይት ልሆንና 7 ልጆች ሊኖሩኝ ይገባኝ ነበር፥ እናም በሞቀ ውኃ ገደልሺኝ።*" ኢዩሊአና ይህን ስትሰማ ደነገጠች፥ "*ጫጩት እንኳን ገድዬ አላውቅም፥ ነገር ግን አንቺ ማነሽ?*" "*እማዬ፥ ያንቺ ልጅ የምሆን ነበርሁ፥ ነገር ግን ተገደልሁ። የአንቺ ጥፋት አልነበረም፥ ጌታ ይህን ያውቀዋል።*" ይህ እንዴት እንደተፈፀመ አብራራች። በስጋጃ መስሪያው ፋብሪካ ስትሠራ፥ (በሌሊት ፈረቃ ነበር የምትሠራው) መብራት ጠፋ። ሁሉም ከመሄዱ በፊት ገላውን ለመታጠብ ተሯሯጠ። (ሴቶች የግላቸው ገላ መታጠቢያ ቦታ ነበራቸው) ሴት የሥራ ባልደረቦቿ ኢዩሊኣና እንደገና እንዳረገዘች አዩ። 7 ልጆች ነበሯት። ሌሎቹ ሴቶች አንድ ወይም ቢበዛ ሁለት ልጆች ብቻ ነበሯቸው። ሌላ ላጅ በማርገዟ ይቀልዱባት ነበር። "*ወደ ሙቅ ውኃው ወስደን ይህን ልጅ እናስወግደው፥ 7 ልጆች አሏት አይበቃትም?*" እያሉ ይዘባበቱባት ነበር። ከጥቂት ቀናት በኋላ የሆነ ችግር እንደተፈጠረ አስተዋለች። ለራሷም ጤንነት አይሰማትም ነበር። በዚያን ወቅት ጽንሱ አድጋ ነቢይት ልትሆን እንዲገባት አታውቅም ነበር።

አሁን ሕፃኗ በሥራ ቦታዋ የሚገኙት ሴቶች እጅ ልጇን እንዴት እንደገደለባት አሳየቻት። ኢዩሊአና ልጇን ሔዋን ብላ ጠራቻትና ስለሆነው ነገር ይቅርታ ጠየቀቻት። ከዚያም ሔዋንን፥ "*ያሳደገሽና እንድታድጊ የረዳሽ ማንነው?*" ብላ ጠየቀቻት። ሔዋንም መለሰች፥ "***ኢየሱስ***" በዚህ ጊዜ የኢየሱስን እጅ ማየት ይቻላት ነበር።

ወተት ከእጆቹ ይፈስ ነበር፥ እናም በአንድ ጊዜ 10 ሕፃናትን ይመግብ ነበር። ቅድስት ማርያም ወይም ቴሬሳ አልነበሩም፥ ነገር ግን ኢየሱስ ነበር በምድር ሰዎች ያልፈለጓቸውን ልጆች የሚመግበው።

ሔዋንን ይቅር እንድትላት ጠየቀቻት። "*ይቅር ብዬሻለሁ እማዬ፥ ነገር ግን እኔ እወልዳቸው የነበሩት ልጆች ይቅር ይበሉሽ አይበሉሽ አላውቅም።*" (ሔዋን 7 ወንዶች ልጆች ይኖሯት ነበር) ትወልዳቸው ይገባ የነበሩትን ልጆች አያታቸውን ይቅር ይሏት እንደሆነ ጠየቀቻቸው። መልሳቸው "*አይ*" ነበር። "አይ" የሚሉትን ቃላት እንደሰማች፥ ወደ ግራው በኩል እንደምትሄድ እርግጠኛ ነበረች፥ ያም ሲያል ነበር።

አሁን ሊፈረድባት ነው። እንደ መድረክ ያለ ከፍ ያለ ጠረጴዛ ነበር። ከዚህ ጠረጴዛ ጀርባ 7 ዳኞች ነበሩ። በጣም ጨካኞች ነበሩ። በቁጣ አፈጠጡባት። ጨለማ ነበር። በዚያ የነበረው ብቸኛው ብርሃን በቦታው የነበሩት አንዳንድ ችቦዎች ነበሩ። ሰይጣን ስሟን ከመጸሐፉ ላይ እስኪፈልግ ድረስ ችቦውን ዝቅ እንዲያደርጉለት አዘዘ። በሚሊየኖች የሚቆጠሩ ስሞች በውስጣቸው የተጻፉባቸው ብዙ መጽሐፍት ነበሩ። ሰይጣን ስሟን ሦስት ጊዜ ፈለገው፥ ነገር ግን ሊያገኘው አልቻለም። በቁጣ አፍጥጠባት ነበር። የሁሉንም ሰው ስም በመጽሐፎቹ ላይ እንዲሆን ይፈልጋል። በዚህ ጊዜ በጣም ፈርታ ነበር፥ ስለዚህም ራሷን ሳተች። ሁሉም በዚህ ደረጃ ላይ ራሳቸውን ይስታሉ። ሁሉም ሰዎች ያለቅሱና ጥርሳቸውን ያፋጩ ነበር።

ቀጥሎ የምታስታውሰው ነገር የሆነ እጅ እንዳነሳት ነው። ኢየሱስ እንደሆነ አውቃው ነበር። በመስቀሉ ቦታ ነበሩ። 3 መስቀሎችን አየች፥ አንድ አንድ በኢየሱስ በሁለቱም ጎን። ከኢየሱስ መስቀል በታች ደምን ተመለከተች። ሚስማሮቹን በእግሮቹ ውስጥ አየቻቸው። ኢየሱስም እንዲህ አላት፡ "***እነዚህን ሁሉ አደረግሁ ኢዩሊአና፥ ስለአንቺ ሁሉንም ነገር አውቃለሁ። ወደ ምድር ተመለሺና ለሁሉም ንስሐ እንዲገቡ ንገሪያቸው። በቶሎ ነው የምመጣው። እያንዳንዱን እንደሥራው እከፍለዋለሁ።***"

ከዚህ በኋላ ራሷን ሳተች። በአስክሬን ማቆያው ውስጥ ነቃች። በሬሳ ማቆያ ውስጥ ለ2 ቀናት ነበረች። በ3ኛው ቀን ስለአሟሟቷ የሬሳ ምርመራ (autopsy) ሊደረግባት ነበር። የሬሳ ምርመራው በሮማኒያ የነፃነት ቀን ምክንያት ነው የዘገየው። (ኦገስት 23) በኮሚውኒዚም ጊዜ፥ በዚያ ቀን ማንም አልሠራም።

በዚህ ጊዜ፥ ጡረታ የወጣ የባፕቲስት መጋቢ (ፓስተር) በሌሊት ህልምን አለመ የሚያስጠነቅቀውንም ድምፅ ሰማ፥ "***ወደ ሆስፒታል ፈጥነህ ሂድ። በዚያም አንድ ሴት አለች። የሬሳ ምርመራ እንዲያደርጉባት አትፍቀድ ምክንያቱም ለእርሷ አላማ አለኝ።***" ወደ ሆስፒታል ሄዶ ለሀኪሞቹ ስለህልሙ ነገራቸው። እንዲህም አላቸው፥ "*ምንም ባታምኑ፥ እስኪ እንጸልይ።*" በዚያ 18 ሀኪሞች በጋራ ነበሩ። መጸለይ ጀመሩ። ኢዩሊአና ከተነሳች በኋላ፥ ለ4 ደቂቃዎች ያህል ተናገረች። (በ**መንፈስ ቅዱስ** ነበር የተናገረችው) መጋቢው የሆነ ሰው የተናገረችውን ቃላት እንዲመዘግብ ጠየቀ። መጋቢው ጠየቃት፥ "*የት ነበርሽ?*" እርሷም "*በጌታ ሀገር*" ብላ መለሰች። "*በዚያ ምን አየሽ?*" እርሷም መልሳ "*እጅግ የተዋበ ቦታ። ዓይኖቼ እንደዚህ ያለ ውብ ቦታ አይተው አያውቁም። የወርቅ መንገዶች፥ ሚሊየኖች መላእክቶች፥ ቅዱሳኑን፥ የጌታን ጠረጴዛ። ሲያልን አየሁ፥ በጣም በጣም አስከፊ ቦታ። **ኢየሱስ** እንዲህ አለ፡ '**ስለሁሉም ነው የሞትሁት።**' በጣም ጥቂቶች ናቸው ወደ ቀኝ (ገነት) የሚሄዱት። በጣም ብዙ ቁጥር ወደ ግራ (ሲያል)። **ኢየሱስ** እስካሁን ስለእኛ እያለቀሰ ነው፥ ስለኃጢአታችን። በአጠቃላይ የሞተችው ለ7 ቀናት ነበር።*"

በሁለተኛው ጊዜ ለ5 ሰዓታት ነበር የሞተችው። በዚህ ጊዜ ደግሞ በአግባቡ ባለመብላት ደክማ ነበር። ተሰልፋ ወረፋ እየጠበቀች ሳለ ራሷን ሳተችና በሸቀጣሸቀጥ መደብር አጠገብ ሞተች። ወደ ሆስፒታል ወሰዷት። በዚህ ጊዜ ገነትን በድጋሚ አየች። ኢየሱስን አየች። በጣም አዝኖ ነበር። ነጩ ልብሱ በደም ተሸፍኖ ነበር። እያለቀሰ ነበር። ኢየሱስ እንዲህ ብሎ ነገራት፥ "***በድጋሚ ወደ ምድር ተመለሺና ለሰዎች ንስሐ እንዲገቡ ንገሪያቸው። በቶሎ ነው የምመጣው። የዓለም ኃጢአት ወደ አብ ደርሷል።***" ኢዩሊአና ኢየሱስ እንድትመለስ ሲነግራት ደስታ ተሰማት። ምክንያቱም ኢየሱስ ውሳኔን እንድትወስን ሌላ እድል እንደሰጣት ያውቅ ነበር።

በዚያው ቀን፥ የልጅ ልጇ እየፈለጋት ነበር። ከጎረቤት ኢዩሊአና በድጋሚ እንደሞተች ተነገረው።

በዚህ ጊዜ ከሞት ስትነሣ፥ በሬሳ ማቆያ ውስጥ ነበረች። በቆሻሻ ገንዳ ውስጥ ልብሷን ትፈልግ ነበር። ቀሚሷንና፥ የአንድ የሞተ ሰውን ጫማ አገኘች። ሻርፗን ግን ልታገኘው አልቻለችም፥ ስለዚህም ከመጋረጃው ላይ ቁራጭ ወስዳ ራሷን(ጸጉሯን) ሸፈነች።

በሬሳ ክፍሉ ውስጥ በሩ ተቆልፎ ነበር። አንድ ሰው በሩን እንዲከፍትላት ትጮህ ነበር። “*በሩን ክፈቱት። ኢየሱስ ለሁሉም ሰው ንስሐ እንዲገቡ፥ እርስ በእርሳቸውም እንዲዋደዱ እንድናገር ልኮኛል።*”

አንዲት ነርስ ድምጿን ሰምታ ስለሁኔታው ለሀኪሙ ነገረችው። ሀኪሙም “*እዚያ ውስጥ ያሉት ሁሉም የሞቱ ናቸው፥ ሊናገሩ አይችሉም።*” አላት። “*አይደለም ዶክተር ፈጥነህ ና፥ በዚያ የአንዲት ሴት ድምፅ ይሰማል።*” በሩን ከፈቱላት። ሲያዩአት ደንግጠው ነበር። በጣታቸው አማተቡ። (ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች የሆነ እንግዳ ነገር ሲፈጠር እንደዛ ያደርጋሉ) ቆዳዋ ገርጥቷል። ወደ ንግድ ቦታቸው ሄደችና ለሁሉም “*ኢየሱስ በቅርቡ ይመጣል፥ ንስሐ ግቡ!*” ብላ ጮኸች።

ወደ ቤቷ ስትመለስ፥ ብዙ ሰዎች ተከተሏት። አንድ ፖሊስ ለጋዜጣ ፎቶ አነሳት። የልጅ ልጇ መጣ፥ በድጋሚ ከሞት መነሳቷን በሰማ ጊዜ ሊያምን አልቻለም። “*አያቴ፥ በድጋሚ ተነሳሽ?*” ከዚያም ራሱን ስቶ ወደቀ። የሆነ ሰው ውኃ ረጨው። ለኢዩሊአና የሬሳ ሳጥኗን ወደ ሆስፒታል እንደወሰዱና ከዚያ ሮጠው እንደሸሹ ነገራት። ከዚያም ፈርቶ ስለነበር ሊጎበኛት ተመልሶ አልመጣም።

**ጌታ ይባርካችሁ ወንድሞችና እህቶች። ንስሐ ግቡ። መንፈስ ቅዱስ ይርዳችሁ። ኢየሱስ እንደሚወደን እርስ በራሳችሁ ተዋደዱ። አሜን።**

## አጋዥ ጥቅሶች

1ዮሐ.2:15-17 *ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም። ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል።*

ሉቃ16:22-25 *ድሀውም ሞተ፥ መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት፤ ባለ ጠጋው ደግሞ ሞተና ተቀበረ። በሲኦልም በሥቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ አልዓዛርንም በእቅፉ። እርሱም እየጮኸ። አብርሃም አባት ሆይ፥ ማረኝ፥ በዚህ ነበልባል እሣቀያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ መላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ። አብርሃም ግን። ልጄ ሆይ፥ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፤ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል አንተም ትሣቀያለህ።*

ማቴ. 4:17 *ከዚያ ዘመን ጀምሮ ኢየሱስ፦ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ ይሰብክ ጀመር።*

1ዮሐንስ.3:11 *ከመጀመሪያ የሰማችኋት መልእክት። እርስ በርሳችን እንዋደድ የምትል ይህች ናትና፤*

1ዮሐ.3:16-18 *እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና በዚህ ፍቅርን አውቀናል፤ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል። ነገር ግን የዚህ ዓለም ገንዘብ ያለው፥ ወንድሙም የሚያስፈልገው ሲያጣ አይቶ ያልራራለት ማንም ቢሆን፥ የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል? ልጆቼ ሆይ፥ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ።*

ገላትያ.1:3-4 *ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን። ክፉ ከሆነ ከአሁኑ ዓለም ያድነን ዘንድ እንደ አምላካችንና እንደ አባታችን ፈቃድ ስለ ኃጢአታችን ራሱን ሰጠ።*

ኤፌሶን 5:1-3 *እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ፥ ክርስቶስም ደግሞ እንደ ወደዳችሁ ለእግዚአብሔርም የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባንና መሥዋዕትን አድርጎ ስለ እናንተ ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ በፍቅር ተመላለሱ። ለቅዱሳን እንደሚገባ ግን ዝሙትና ርኵሰት ሁሉ ወይም መመኘት በእናንተ ዘንድ ከቶ አይሰማ፤*

1 ጢሞቴዎስ.2:6 *ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ፥ ይህም በገዛ ዘመኑ ምስክርነቱ ነበረ፤*

የጌታችንና የመድኃኒታችን የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነት ቅዱስ ወንጌል በዮሐንስ 14:1-7 *ልባችሁ አይታወክ፥ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ። በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፥ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ። ወደምሄድበትም ታውቃላችሁ፥ መንገዱንም ታውቃላችሁ። ቶማስም:- ጌታ ሆይ፥ ወደምትሄድበት አናውቅም እንዴትስ መንገዱን እናውቃለን? አለው። ኢየሱስም:- እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም። እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር። ከአሁንም ጀምራችሁ ታውቁታላችሁ አይታችሁትማል አለው።*

ራእይ. 22:12 *እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፥ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።*

*በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥ አሜን።*
*ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ።* Translated to Amharic by Muluneh Addisu, shalommuluneh@gmail.com